# በሳውዲ አረቢያ የተደበቁ እውነቶች !

## ወደ አረብ ሃገራት የተስፋ ምድር የሚደረገው ጉዞና አሰቃቂው ፍጻሜ !

ክፍል 7

ነቢዩ ሲራክ- ከሳውዲ አረቢያ

## እግረ መንገድ . . .

በክፍል 6 ሰበር ሰሞነኛ መጣጥፌ አረቦች "የቀይ ባህሯን ፈርጥ ሙሽራ " እያሉ በሚያንቆለጳጵሷትን የቀይ ባህር ወደብና የኢንዱስትሪዋ ማዕከል የሆነችውን ጅዳን ስላጥለቀለቀው ዝናብና የጎርፍ ናዳ ያላያችሁት ለማሳያት ያደረግኩት ሙከራ ረድቷችሁ ከሆነ መልካም ነው. . . በጸሐይ መግቢያ በኩል በከተማዋ የተጠመጠመው ትልቁ ቀይ ባህር የፈነዳን ያህል ለሰአታት የዘነበ ዝናብ የከተማዋን ሁለንተናዊ እንቅስቃሴ ለቀናት ማሰናከሉ በእርግጥም ከተማዋ ካላት አለም አቀፍ ስምና ዝና አንጻር ሲታይ ያሳዝናል. . . ያሳፍራልም ! 3.5 ሚሊዮች የምንገመት በጅዳ የከተምን የሁሉም ሃገር ዜጎች በዚህ መሰሉ ድንገተኛ አደጋ ከፍቶናል ! ትልቋን ከተማ ትንሽ ያደረገው ይህ ችግር ተቀርፎ ለማየት ያብቃን በማለት ጸሎትም ተስፋም በማድረግ ለትውስታ ያህል የት እንዳቆምኩ ማስታወስ ከቻል ኩ ወደ ዛሬው ርእሰ ጉዳይ ላምራ. . . የዛሬውን ጽሁፍ የምቀጥለው የጅዳን ጎርብ ያዘከርኩበትን የክፍል ስድስትን ሰበር ወጋወጌን ከዘለላችሁ በኋላ በክፍል አምስት ሃገረ ጀርመን ቦን ከተማ ሁኜ በሳውዲ እስር ቤቶች ሆነው ስለሞቱትና በስቅየት ላይ ስላሉት ወገኖች ማንሳቴን አትረሱትም፡፡ ዛሬም ከዚሁ በመቀጠል ጉዳዩን የደረሰበትን ለማወቅና መረጃ ለማግኘት ፍለጋ ስንቀሳቀስ ያጋጠመኝን ከማነሳበት ክፍል ደርሻለሁና ተከተሉኝ . . .



የተስፋዋ ምድር መዳረሻ. . .

እኔና ጋዜጠኛ ጎይቶም ቢሆን ሲነጋ ወደ ስልጠና ሲመሽ በኒያ የገና ገበያዎች በደመቁት የቦን የሜዳ ላይ ገበያዎች ስንዘዋወር ማምሸቱን ለምደነዋል፡፡ የምናየው የምንሰማው እንግዳ ሲሆንብንና አልገባን ሲል እየተቁለጨለጭን ፤ ሲገባን እየተሳሳቅን ወሬያችን በቀዝቃዛው ቢራ እያወራረድን ስንዝናና እናመሻለን ! እንዲያም ሲል የኛዋን ቁንድፍት አረቂ በምትመስለውን "ተኪላዋን" ፉት እያደረግን ብርዱን ለመቋቋማችን ሙከራ ማድረጋችን አልቀረም፡፡. . . መቸም ጥርስ ከማያስከድነው ከጋዜጠኛ ጎይቶም ጋር መለየት አይመችም. . . እሱም ወንድም እህቶቻችን ለተሻለ ኑሮ ፍለጋ ከሞት ጋር ከሚደረገው ወደ አረብ ሃገራት የተስፋ ምድር በሚያደርጉት የባህርና የበርሃውን ጉዞ ከአይን ምስክሮች የሰማሁትን አጫውተዋለሁ፡፡ አንዳንዴ ደግሞ ከችግር መከራው ወጥቶ ስለ ከተማው ቀልድና ጫዎታ ስለምዎጋው ጎይቶም የኔን ጫዎታ ይወደዋል፡፡ በሚያሳዝነው እየተከፋን ፤በሚያስቀው እየተዝናናን የሆድ የሆዳችን ስናዎራ ስንከርም "ጓድ" ጎይቶም እንደኔው ቢያመሽ እንጂ በጊዜ ወደ መኝታ ክፍሉ መግባትን አይወድም፡፡ ብቻ አንዳንዴ ስንጨዋዎት ሰአቱ ሳናስበው ጥርግ ብሎ ይሄዳል፡፡ አንዳንዴም እያወቅነው እስከ እኩለ ሌሊት ድረስ አመሻሽተን የመኝታ ሰአት ሲደርስ ቅር እያለን ሳልወድ በግድ እንለያያለን፡፡ ፈረንጆቹ አስተናጋጆች አፍ ላፍ ገጥመን ስናዎራ እንደነሱው ሃገር "ምናምን" የወንድ ጓደኞች እየመሰላቸው በፍቅራችን የቀኑ ያህል አፍጥጠው


አሰቃቂው የቀይ ባህር ጉዞ. . .

በመገረም ይመለከቱናል " ደህና ሁን " " ደህና ሁን"ተባብለን ስንለያይና ይመለከቱና ደግሞ ግራ ይገባቸዋል! ይህ አስተያየታቸው ያልተመቸኝ እኔ ብቻ አይደለሁም፤ "ጓድ" ጎይቶምንም ጭምር እንጅ ! አንድ ቀን ግን ነገሩ አላምር ሲለው አንዲት በጣም የሚግባባትን ጀርመናዊ ወጣት እንግዳ ተቀባይ ጠጋ ብሎ የወንድሜ ጓደኛ መሆኑንና የአንድ ሃገር ልጆች ግን ዘመንና ፖለቲካ የተለያየን መሆናችን ነግሮ ካሳሳቃት ወዲህ ያንን ጥርጣሬ ሁሉም ትተውታል ! የታላቋ የጀርመን መንግስት ባለስልጣን ከወንድ ጓደኛቸው ጋር ጋብቻ መፈጸማቸው ሳይታፈር በአደባባይ በተነገረበት ሃገር የመኖራችን ያህል የሆቴ ሰራተኞች በኛ ቅርበት መደናገጣቸው ባይገባኝም የሚዋጋ አይና ቸው በጎይቶም በመሰበሩ ተመስገን ማለቴ ግን አልቀረም! አጥንት የሚሰብረውን ብርድ ለመቋቋም ብርድ ልብሱን ደራርቤ የጠባብ የሆቴል ክፍል ማሞቂያ ለኩሼ ፤ራሴን ከአንሶላና ብርድ ልብሱ ውስጥ ሽጉጨ ማስታወሻየን ከፊት አደርግና መሞነጫጨር ጀምሬያለሁ. . . የአረቡ አለም የኛ ኑሮ የተደበቁ እውነቶች የዚያ ሰሞን ውሎ ለዛሬው ጥቂቶችን እነሆ . . .

**pdfMachine**
**Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!**
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

## "መግባት ክልክል ነው !" መልስም የለም !

በሳውዲ አረቢያ የማቆያ እስር ቤት ተገቢ ባልሆነ አያያዝ የሚንገላቱትን ወንድሞቻችንና የመከራው ኑሮ በቃን ወደ ሃገር እንግባ በሚል በሃገሪቱ ፖሊስ ለመያዝ ፈልገው በድልድይ ስር ለወራት ኑሮ ይገፉ የነበሩ ወንድም እህቶቻችን ስቃይ መቀረፍ ይዟል . . . የኢትዮጵያ መንግስት ባለስልጣናትም ወደ ጅዳ እስር ቤት ሄደው መጎብኘትና ጊዜያዊ መተላለፊያው ሊሴ ፓሴ እንዲሰራ በመፍቀዳቸው ችግሩ ረገብ ብሏል . . . በድንበር ከተማዋ በጀዛን የማቆያ እስር ቤቶች በአንጻሩ "የኢትዮጵያውያን ስደተኞች መብታ ችን ሲረገጥ መብታችን የሚያስከብሩልን ዲፕሎማቶች አጣን! " የሚለው የዜጎች ጩኸት ተበራክቷል፡፡ በክፍል አምስት መጣጥፌ እንደገለጽኩት በሳውዲ የድንበር ከተማ በጀዛን የማቆያ እስር ቤት በአያያዝ ጉድለት ህይወታቸው የጠፋ ወንድሞቻችን በሚመለከት የሳውዲ ሰብአዊ መብት ተከራካሪዎችን እማኝ ያደረጉ ጋዜጦችና



ጸሃፍት ሳይቀር በረመዳን አጋማሽ በማቆያ እስር ቤቱ በተፈጠረ ሙቀትና መጨናነቅ አምስት ያህል ኢትዮጵያውያን አሚሚት ይጣራ ዘንድ ጠይቀዋል ! የዚህን ጉዳይ መዳረሻ ለማጣራት በጂዳ የኢትዮጵያ መንግስት ቆንስል ጀኔራል አምባሳደር ተክለአብ ከበደን ጨምሮ ጉዳዩ የሚመለከታቸው የመስሪያ ቤት ከፍተኛ ኃላፊዎችን ለማነጋገር ወደ ቆንስል መስሪያ ቤቱ ጎራ አልኩ፡፡ ከሁሉ በማስቀደም ወደ ሃገር ቤት ለመግባት ለወራት በቂ ድጋፍ ሳይደረግላቸው የጨለማን ኑሮ ከሚገፉባት መጠለያ መልዕክት ደርሶኝ ስለነበር ያንኑ ለማጣራት ወደ ዚያው አቀናሁ፡፡ ከታማሚ ወገኖች ጋር ተቀምጨ እያወጋሁ ሳለ ከአንባሳደሩ ስልክ ተደወለልኝና ወደ ቢሯቸው እንድመጣ ጠየቁኝ . . . የአምባሳደሩ ንግግር ቆጣ የተቀላቀለበት ነበር፡፡ ብዙም ሳልቆይ ወደ አምባሳደሩ ቢሮ አመራሁ፡፡ ወደ እርሳቸው ቢሮ መግባት ደግሞ ቀላል አይደለም፡፡ ካሜራ የተገጠመበት ክፍል በእርሳቸውና በጸሃፊያቸው ቁጥጥር በሚደረግበት በዘመናዊ አውቶማቲክ ቁልፍ ግጥም ተደርጎ ተዘግቷል፡፡ በዋናነት የዜጎችን መብት ለማስጠበቅ የተሰየሙ ሃላፊ በር መዘጋት ብቻም ሳይሆን ግልጋሎት ሊሰጡት ከተሾሙት ማህበረሰብ ጋር ያላቸው የግንኙነት ክፍተት አስገረመኝ፡፡ የሚወጡትና የሚገቡት በጀርባ በር በሆነበት ቆንስር መስሪያ ቤት እኒህ መከረኞች አለብን የሚሉትን ችግራቸውን ለባለስልጣን እንዴት ብለው ሊያሰሙ ይችላሉ ? ስል ከራሴ ጋር አጉረምርሜ ውስጤን ጥሩ ስሜት አልተሰማውም. . . ብቻ በአምባሳደሩ መጠራቴ ለአስተናጋጆች አስታውቄና በውስጥ ስልክ ይሁኝታ ተገኝቶ በእድሜ ጠና ያሉትን እናት የቆንስል ሰራተኛ ወደ አምባሳደሩን ቢሮ መግቢያ በርን በካርድ ቢጤ ነካ አደረጉና ከፍተውልኝ ገባሁ . . . አምባሳደሩ ተሰርፈው ጠበቁኝ ! ራሴን ለማረጋጋት ሞከርኩ . . . " . . . ጋዜጠኛ መሆንክን ረሳህው እንዴ ? ሳታሳውቀን እኮ ወደ ዚህ ግቢ ልትገባ አይገባም! መግባት ክልክል ነው! " አሉ መነጽራቸውን እያስተካከሉና ከወንበራቸው እየተደላደሉ ! በቁጣ የጀመሩት ንግግራቸው ቀጠሉ. . . ዝም ብየ መስማቴን ቀጠልኩ . . .ስገባና ስወጣ ለቆንስል ሃላፊዎች እንዳስታውቅም ገለጹልኝ፡፡ሁሉንም በጸጋ ባልቀበለውም ወደ ስለመ




ጣሁበት በጀዛን እና በጅዳ እስር ቤቶች ስለሞቱት ኢትዮጵያውያን ጉዳይ ከዚህ አስቀድሞ የቆንስል መስሪያ ቤቱ ጉዳዩን እየተከታተለው እንደሆነ በአካል የገለጹልኝ መሆኑን ያን ሰሞን እርሳቸውና ምክት ላቸው ቆንስል ኑረዲን ሙስጠፋን "ልዩ ትኩ ረትና ክትትል እያደር ግንበት ነው" ስላሉኝ ጉዳይና በቆንስሉ ውስጥ ባለው መጠለያ ሆነው ወደ ሃገር ቤት ለመግባት ለወራት ስለሚንገላቱ በሽተኞች ጉዳይ ጠየቅኳቸው፡፡ መልስ ሊሰጡኝ ግን ፈቃደኛ አልሆኑም !

ብቸኛ መረጃ የማገኝበት ቆንስል በስሪያ ቤት በሩ ዘግቶብኛል፡፡ ያን ሰሞን ሰብአዊ መብታቸው ስለተገፈፈ ዜጎች የጸፉ ሃያሲ ሳውዲና የመብት ተከራካሪዎችን ቀርቤ ማነጋገር ጀመርኩ፡፡ በጉዳዩ ብዙ መግፋት እንዳልፈለጉ ተረዳሁ. . .መብት ገፈፋው በመንግስታቸው አንዳንድ ማዕከላት በታየ ደካማ አሰራር የተከሰተ ነውና ችግሩን ማጉላትና ማሳደግ አልፈለጉም ! እነሱ ሃቅ አላቸው. . .! እኔም በአሳር በመከራ ህይወታቸው ያለፉት ቁጥር ብዙ ቢሆንም ሃላፊዎች አምነው በጋዜጣ በይፋ ያወጧቸውን አምስት ያህል ወንድሞቻችን እጣ የማሳወቅ ከዜግነት ያለፈ ሰብአዊ ግዴታ አለብኝና በህሊና እዳ ተቀፍድጃለሁ . . . ዲፕሎማቶቻችንም ቢሆን ህዝብና መንግስት የጣለባቸው የዜጎቻቸውን ደህንነት የመጠበቅ ሃቅና ታላቅ አደራ አለባቸው !

**pdfMachine**
**Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!**
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

ተሚጋች ቢገኝ ኖሮ እንኳንስ እስላማዊውን የሸሪአ ህግ መንግስት በምትከተለው ሃገር ቀርቶ ህገ መንግስት የሌላቸው ሃገራት ቢኖሩ ይህ መሰሉ ወንጀል በሰብእና ላይ የተፈጸመ ኢ-ሰብአዊ ተግባር በመሆኑ ፍትህ የሚገኝበትን መንገድ የሚሸሹት አይሆንም፡፡ ያም ሆኖ በግፉአን ዜጎች ላይ ግፍ ሲፈጸም ከማጋለጥና ፍትህን ከመጠየቅ ይልቅ የዜጎች መብት ጥበቃ በዋናነት የሚመለከታቸው ሃላፊዎች ጉዳዩን ለማድበስበስና ለመሸሸ ከሚደርጉት የሸምጥ ሩጫ እኩል ለመሸምጠጥ አቅሜ የተገደበ ሆኗል . . . ለዚህ መሰሉ አንገብጋቢ ጥያቄ ዛሬ መልሱን ማግኘት ቢገድም ጥያቄውን የሞቱት ወገኖች ቤተሰቦች ፤ መንግስትም ሆነ ጉዳዩ ያገባናል የሚሉ ወገኖች ነገ የሚያነሱት ጥያቄ እንደሚሆን ተስፋየ የጸና ነው፡፡ ከዚህ ብዙ ከሄድኩ አደጋው ሰፊ ነውና በእኔ አቅም ብዙ የሚገፋበት አይደለም. . . የቀረውን ለማድረግ አቅሜ አልፈቀደም . . . ባንድ ወቅት ነጻ በሚባለው ኮሚኒቲ አባልነቴ በስላጣናቸው የገፈፉት ባለስልጣን ይባስ ብሎ ዛሬ በሃገሬ መሬት በሚመሰለው የቆንስል መስሪያ ቤት "ያለ ፈቃድ ገብተሃል " ብለውኛል . . . የወገኖቸን ሮሮ ማቅረብ ማሰማቴ እንደ ትልቅ ጥፋት ተቆጥሮብኛልና ወንጀለኛ አድርገውኛል . . .! የዜግነት ግዳጅን ልወጣ ባልኩ ጎልማሳ ይህ መሰሉ ማፈራሪያ ብዙዎችን ያስገረመ ቢሆንም እኔ የለመድኩት ነውና አይደንቀኝም ! በዚህ ሁኔታ የጀመርኩት የመረጃ ፍለጋ ፍንጭ ቢዘጋጋም በጀዛን እስር ቤቶች የነበሩ የችግሩ ዳፋ ቀማሾችንና በጀዛን ድንበር ስላለቁት ዜጎች ሊያዩት የሚሰቀጥጠው አሰቃቂ የተንቀሳቃሽ ምስል መረጃ ደርሶኛል. . . የሚጣየው ቢሰቀጥጥም በጀሮየ ደጋግሜ የሰማሁትንና ማመን ያቃተኝን ማየት ማየት አስችሎኛልና መረጃው ማግኘቴ አስደስቶኛል ! ይህን በቀጣይ እመለስበታለሁ ከዚያ በፊት ግን በበሺታ ተቀስፈውና በተለያዩ ምክያቶች በቆንስሉ መጠለያ ስለተጠለሉ ወገኖች ስላየሁት በጥቂቱ ላውጋችሁ . . .

## ድጋሜ መስማት ያልቻልኩት አንደበት . . .

. . . የእለት ጉርሴን ለመሙላት ከወዲህ ወዲያ ስባትል አልሳካልህ ብሎ ብዘገይም ከሁለት ቀናት በፊት አንዲት እህት ከበሽተኞች መጠለያ በተንቀሳቃሽ ስልኬ ደውላ መልዕክት ያቀመጠችው እህት ወደ ምትገኝበት መጠለያ ደርሻለሁ፡፡ .በጀዛን የሞቱትን ጉዳየን ለመከታተል ወደ ቆንስል መስሪያ ቤቱ ሃላፊዎች ከማቅናቴ በፊት ነበር ወደ መጠለያዋ የሄድኩት፡፡ ይህች ክፍል ከህዝብ በትብብር በሚሰበሰብ ገንዘብ የተሰራች ስትሆን አልጋና ፍራሽ ያመጡ ቅን አሳቢ አንዳንድ ነዋሪዎች ናቸው፡፡ ከመኪና ማቆሚያው አጠገብ ወደ ተሰራችው መጠለያ እያዘገምኩ ያች እህት ያስቀመጠችውን መልዕክት አስታወስኩት. . . በሰለለ የተማጽኖ ድምጽ ያገኘሁት መልዕክት ቃል በቃል እንዲህ ይላል፡- "ስሜ. . . ይባላል፡፡ከሃገሬ ከመጣሁ ገና ሶስት አመት አልሞላኝም፡፡ በህጋዊ የስራ ኮንትራት ከመጣሁ ጀምሮ በአንድ የአረብ ቤተሰብ ተቀጥሬ ስሰራ ቆየሁ፡፡ የስድስት ወር ደሞዜን ችግረኛ ቤተሰቦቸን አቅመ ደካማነት አስረድቻቸው ደመዎዜን ተቀብየ ለቤተሰቦቸ ልኪያለሁ. . . ብርድ መትቶኝ በጠና ታመምኩና ጥቂት ካሳከሙኝ በኋላ ሲጠናብኝ ወደማውቃቸው ሃበሾች ቤት ወስደው ጣሉኝ፡፡ እነሱም እመም ሲጸናብኝና ወደ ሃኪም ቤት ለመውሰድ አቅሙ ስለሌላቸው ብዙ ከጣሩልኝ በኋላ ሲቸግራቸው እዚህ አምጥተው ጣሉኝ ! አላህ ይስጣቸው እነሱ ሞክረውልኛል . . . ታሪኬ ብዙ ነው፡፡ አሰሪዎቸ ቀርበው የቀረብኝን ደመዎዝና ፓስፖርቴን እንዲሰጡኝ ያልካልጀነ ወደ ሃገር ቤት ለመሄድ ሊሴ ፓሴ እንዲሰራልኝ ሃላፊዎችን ጠይቄ እሽ ብለውኝ ነበር፡፡ አሁን ግን ሰለቸኋቸው ረሱኝ መሰል ይህው ሶስተኛ ወር ሊሞላው ነው የሚጓተትበት ነገር አልገባኝም. . . ደግሞም ታምሜያለሁ ! አንተ ደግሞ ጋዜጠኛ ነህ አሉ. . . ከቻልክ እዚህ እመጠለያው ናና ላነጋግርህ . . . አላህ ይስጥልኝ " ስሜትን የሚነካና የሚያውክ ድምጽ ነበር . . .




የመጠለያውን ገርገብ ያለ በር ሰላምታ እያቀረብኩ ከፍቸ ገባሁ. . . በበርሃ ንዳድና በከፍተኛ የውስጥ ደዌ በበሺታ የሚሰቃይ ወንድም እንደከበሮ የተወጠረው ሆዱን እያሻሸ ፤ በበሺታ የደከመች እህት ልታየኝ እያፈረች ፤ የግመል በሺታ አጠቃው የተባለና አጎንብሶ የሚሄድ ወንድንም ከአልጋ ላይ ቁጢጥ ብሎና ጤነኛ መስሎ ፤ ጀርባውን በጥይት እንደቆሰለ የተነገረኝና በቆንስሉ ትዕዛዝ ከጀዛን እንደመጣ አስቀድሜ የሰማሁት ወጣት ምርኩዙን ከጎኑ አጋድሞና አንድ ታማሚዎችን ጠያቂ እህት በጠባቧ ተኮልኩለዋል፡፡ መልዕክት ያስቀመጠችልኝ ልጅ እንዳለች ሳጫውተው ስልኩን የሰጣት እሱ እንደሆነ የገለጸልኝ ወንድም ያችን እህት ባይኑ አመላከተኝ፡፡ ከተጋደመችበት ሆና ሾርባ ቢጤ ስትቀማምስ የነበረውን አቁማ ተስተካክላ

**pdfMachine**
**Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!**
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

ለመቀመጥ ሞከረች. . . እህቴ በሰለከላካው አፍንጫዋ ዳር ዳር እንባ ያነጣው የሚመስለው ፊቷ የደም ግባት ሸሽቶት ከጎደጎደው አይኗ ጋር ያስደነግጣል . . . ብል የበላው የመሰለው ጸጉርዋ መሳሳቱን ከጠመጠመችው ጥቁር ሻሽ እልፎ ይስተዋላል፡፡ በስላሙ ጊዜ የሚያውቁዋት የሃገሯ ልጆች ያመጡላትን ሾርባ ለመቀማመስ ከራሷ ጋር ትታገላለች . . . ሾርባዋን ትጨርስ ዘንድ ልትጠይቃት የመጣችው እህት ተንበርክካ ትማጸናታለች! ነብሱዋን ለማሰንበት ስትታገል ደርሻለሁና ቀና ብላ ተመለከተችኝ ! ቁልጭልጭ እያለች ከማየት አይኗን ሰበር እያደረገች ትተክዛለች! በውስጧ ማልቀሷ በውስጤ የሚብረከረክ ሆዴን አባባው . . . እኛ ከማዘን እሷ ከማልቀስ ባለፈ ግን ምንም ማድረግ አይቻለንም ! ቀና እያለች ታየኛለች. . . ሁሉም ታማሚዎች አንዴ እሷን አንዴ እኔን ይመለከታሉ ! ግራ ተጋባሁ. . . ከነጣው ሸሚዜ ላይ ያንጠለጠልኩት ትቁር መስመር ያለበት ቀይ እራፊ ከረባት የቆንስል ሃላፊ አስመሰለኝ መሰል የታማሚዎች ችግራቸውን ለመግለጽ ልባቸው መቆሙን ከጎኔ የቆመው የሚያውቀኝ ወንድም አጫዎተኝ ! ከጠና ህመሙ በወገን እርዳታ ተርፎ በማገገም ላይ ያለው ከዚያ ድልድዩ ስር የማውቀው ወንድም ሙስጦፋ ነበር ይህንን ሹክ ያለኝ ! የቆንስል ሰዎች አይጎበኟችሁም ? ብየ መጠየቄ አልቀረም፡፡ መልሱ በአይናቸውና በአንገታቸው ደረሰኝ . . . በዚህ ዙርያ ብዙ መሄድና ስሜታቸውን መጉዳት አልፈለግኩምና ጥያቄየን አቆምኩ! ሁሉም ያሳዝናሉ . . . ቀልቤን የሳበችው ግን ባለ መልዕክቷ አሳዛኝ እህቴ ነበረችና ፊቴን ወደ እርሷ አዞርኩ ! ደጋግማ ተመለከተኛለች . . . ከሁለት ቀናት በፊት መልዕክት ያስቀመጠችልኝ ወንድም ከፊትዋ ላይ እንደቆምኩ ግን አልገባትም. . . ያስቀመጥሺው ስምሽ እውነተኛ ስምሺ ነው ወይስ የፓስፖርት ስምሽ ? ብየ ለማነጋገር ስጀምር. . . ከቅርብ ርቀት የሚደግፋት ሌላው ታማሚ ወንድም ". . . አሁንማ አትናገርምኮ. . . መስማት ግን የምትሰማ ይመስለኛል ! " ሲል አጫወተኝ፡፡ የምትናገርና የምትሰማኝ እንጂ የአንደበቱዋን መዘጋት አላወቅኩምና ደነገጥኩ ! አሁንም በጥያቄ ማጨናነቅ አልፈለግኩም . . . ያ የሰማሁት ድምጽ የለም . . . የትናንቱ ልሳንና አንደበት ተዘግቷል ! ማንነቴን ነግሬ ደግሞ በጸጸት ላደብናት አልፈለግኩምና ልቤ በሃዘን ተሰብሮ ተለየኋት !

## ግመል እረኛና ተምር ለቃሚዎቹ ሃበሾች . . .

ከበሽተኞች መጠለያ ሳልወጣ ወደ ሌላኛው ታማሚ ወንድሜ ፊቴን ሳዞር ከአልጋ ላይ ቁጡጥ ብሎ የነበረው ሌላ ወንድም ሊሸኘኝ ከአልጋው ለመውረድ ሲንቆራጠጥ አየሁት. . . ቀስ እያልኩ እግሬን ከዚያች የመከራ ድባብ ካጠላባት ቤት ነቅየ ወጣሁ. . . እየተከተለኝ እንደሁ ላረጋግጥ ዘውር ስል ያየሁትን ማመን አቃተኝ፡፡ ያ ወንድም ከተቀመጠበት እንደ መነሳት ብሎ መልሶ ተጎንብሶ የእግሮቹን መታጠፊያ በሁለት እጆቹ ግጥም አድርጎ ይዞ አንገቱን ቀና አድርጎ ተከተለኝ፡፡ ያየሁትን ማመን አቃተኝ፡፡ በእርግጥም ተቀምጦ ሲያዩት የታመመ አይመስልም፡፡ እኔም የጭንቀቴን ያህል እንደ ማጎንበስ እያልኩ ጥሩ ቀን ይመጣል የሚል ተስፋ እየሰጠሁት ብዙ አዎጋን . . . የመጣው ከገጠሪቱ የሃገራችን ክፍል በመሆኑ ሙቀቱ እንጅ



ከብት፤ በግና ፍየን እረኝነቱ የግመል መጠበቁን አልጠ ላውም፡፡ የበርሃው የግመል እረኝነት የስደት ህይወቱን ባይቀይረውም የሚያገኛትን ከ200 ዶላር የማትደርስ ደመወዝ ሃገር ቤት ላሉ አባት ፤እናት፤ ወንድምና እህቶቹን ህይወት ግን ለውጣለች፡፡ ይህ በመሆኑ ፈጣሪውን አመስግኖ ይኖራል ! ከእለታት አንድ ቀን ግን ሳያስብ ሳያልመው ጎኑን ህመም ተሰማው. . . እየቆየ እየቆየ ህመሙ ጀርባው ድረስ ዘልቆ ሄደና ሽንጡን እየሳበ አስጎንብሶ አስኬደው ! ህክምና ማግኘት ቀርቶ ስለህክምና ማሰብ በሚችልበት ሁኔታ አይደለምና ያለው አማራጭ ወገኖቹን የሚደግፍበትን ስራ ትቶ ወደ ሃገር ቤት መመለስ ብቻ ሆነ፡፡ እናም በሁለት እጆቹ እግሮቹን ግጥም አድርጎ በመያዝ አንገቱን ቀና አድርጎ ሲሄድ እየደከመውም ቢሆን ሁኔታውን ባዩ ወገኖች ሰብአዊ እርዳታ ታክሎበት ጅዳ ደረሰ . . . የሚያውቁት የሃገሩ ልጆች በሰው በሰው ብለው ወደ መንግስት ሆስፒታል ቢያስገቡትም የአቅም ጉዳይ ሆነና በቂ ህክምና ሊያሰጡት ግን አልቻሉም . . .የሚችሉትን ያህል ግን ሞከርሩለት . . . የመጣው በባህር በመሆኑና ማንነቱን የሚገልጽ ምንም መታዎቂያ አለመያዙም ሌላው ችግር ሆነ ! ሃኪሞች ምንም እንኳን ህመሙ አስጊና አደገኛ መሆኑን ቢረዱም ሰው ከጎኑ የለውምና ከገባበት ሆስፒታል በግዳጅ አስዎጡት . . . መላ ጠፋው ጨነቀው ! መላ ይገኝ ዘንድ ኪሱን ደባብሶ ለታክሲ የሚሆን ብር አገኘና እያጠያየቀ በታክሲ ወደ ኢትዮጵያ ቆንስል አመራ ! በዚያው በሚገኘው የኮሚኒቲ ካፍቴሪያ እንደደረሰ የተጨናነቀውን ፊቱንና አጎንብሶ ሲሄድ

**pdfMachine**
**Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!**
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!

የተመለከቱት አዘኑ . . . በካፍቴሪያው ሰራተኞችና የሚስተናገዱ ነዋሪዎች ሁሉም አፍጥጠው ተመለከቱት. . . ወደ ካፍቴሪያው ሲገባና ሲዎጣ የሃገሩ ልጆች ጠረጴዛ ከበው ተቀምጠው የሃገራቸውን ቴሌቪዥን እየተመለከቱ ሲጨዋዎቱ እሱ በበሺታ ተቀስፎ ማየት በመቻሉ ፈጣሪውን አላማረረም . . . በሽታው የለቀቀውን ያህል ተሰማው እንጂ ! ሁሉም ከንፈራቸውን እየመጠጡ ይመለከቱታል ! ቆሞ ሲራመድ እንጅ ሲቀመጥ ታማሚ አይመስልም. . .አንዳንዶች ጠጋ እያሉ የሆነውን ይጠይቁታል፡፡ ልጅነት በሚነበብበት ፊቱ ላይ ፈገግታን እየነሰነሰ ያጫውታቸዋል ! የቻሉት አበረታተው ገንዘብ ቢጤ ሽጎጥ ሲያደርጉለት የቀሩት የሚበላና የሚጠጣ ሳይቀር ይጋብዙታል፡፡ ያንን አጋጣሚ አይረሳውማና እየተፍለቀለቀ አጫዊተኝ ወደ ቆንስሉ በመጣበት አጋጣሚ ስማቸው ወንድም ምናሴ ወንድም ዮሃንስ(ጆን) የሚባሉ ኢትዮጵያውያን ወንድሞች እንዳገኘ ገለጸልኝ. . . ስማቸውን ሲጠራልኝ ወዲያው ገባኝ ! ታሪኩን ይነግረኝ ቀጠለ . . .ምናሴና ዮሃንስ አብረው የሚበላና የሚጠጣውን ከቀማመሱ በኋላ እንደተለመደው ሙሉ ታሪኩን አጫወታቸው . . . አልባሌ መስለው የቀረቡት ወንድሞች በእርግጥም በግል ስራ የሚተዳደሩ፤ በባህር ሳይሆን በቦሌ በኩል የመጡ ፤ በህጋዊ መንገድ መጥተው በህጋዊ መኖሪያ ፈቃድ የሚኖሩ አልመሰለውም ! ወንድሜ ከድሃ አባቶች ፤ የታመመ አሳካሚዎች ፤ ከሞተ ቀባሪ ወንድሞች እጅ መውደቁ አልገባውም ! ደግሞም ሲያዩዋቸው ያን የሚያደርጉ አይመስሉም ! ያም ሆኖ በተደጋጋሚ የወገን አለኝታ መሆናቸውን አሳይተዋል . . . አቅማቸው ባይፈቅድም በግል ተነሳስተው ከወገኖቻቸው አልፈው አረብ ሰብአዊ እርዳታ አድራጊዎችን እያስፈላለጉ አቅም ያጡና ወደ ቆንስል መስሪያ ቤት የተወረወሩትን እንደሚደግፉ በቂ መረጃ ነበረኝና በጥሩ እጆች መውደቁ ተሰማኝ . . . እናም እህ እያልኩ መስማቴን ቀጠልኩ . . . ብዙም ሳይቆይ እጁን ይዘውት ወደ ቆንስል መስሪያ ቤቱ ወስደው ባሳር በመከራ መጠለያ እንዳስፈቀዱለትና ህክምናም እንዳስጀመሩለት አጫወተኝ . . . አሁን መድሃኒት መውሰድ በመጀመሩ ከላይ በተገለጹት ወንድሞች ቅርብ ክትትልና እርዳታ እንደተሻለው ደስታውን መቆጣጠር እያቃተው እንባውን ካይኑ እያረገፈ ገለጸልኝ . . .

ባንድ ወቅት "ሃፍል አልበጠን" በተባለ የሳውዲ ግዛት ያጋጠመኝ ታሪክ ባይኔ መጣ፡፡ ጊዜው ከአመት በፊት ነው፡፡ ከስራ ባልረቦቸ ጋር "ሃፍል አልበጠን" ወደ ሚባለው የሃገሪቱ ምስራቃዊ ክፍል ለስራ ጉዳይ ከስራ ባልደረቦቸ ጋር ሄጀ ያጋጠመኝ ፍጹም አይረሳኝም፡፡ ዬለት ስራችን እንደጨረስን የ600 ትሬላ ባለቤት ከሆነው የሳውዲ ቱጃር ቤት ምሳ ተጋበዝን፡፡ ቦታው ከከተማዋ ወጣ ወዳለው የቱጃሩ የመኖሪያ ቤት ነበር፡፡ "መንዲ"የሚሉት የአረቦች ባህላዊ ሩዝ ቀርቦልን ሞልቶ በተረ ፈው ተሻምተን በልተን እንደጨረስን በሰፊው የተንጣለለውን የባለሃብቱን የተምር ማሳና የግመል እርባታና ከባልደረቦቸ ጋር እንድን ጎበኝ ተጋበዝን፡፡ በዚህ አጋጣሚ የሆንኩና ያጋጠመኝን አሁን ድረስ ሳስታውሰው ዛሬ ድረስ ውስጤን የሚሰማው አንዳች ስሜት አለ . . . በዚያ ማሳ ግመሎችን የሚያሰማሩትና ከተምር ዛፉ በመሰላል ተንጠላጥለው ተምር የሚለቅሙት እድሜያቸው ከሃያ የማያልፍ የሚያማምሩ ጠያይም ሴት የሃበሻ ልጆች ነበሩ . . .የማልጠብቀውና አስደንጋጭ ! . . . እኔም በዚያ ደረጃ መምጣቴ ግራ የገባቸውን እህቶቸን ጠጋ ብየ አጫወትኳቸው. . . የሚገርመው ወደ ሳውዲ የመጡት በህጋዊ መንገድ ሲሆን ከደላላ ደላላ ተቀባብሏቸው ከተምር ለቀማና ለግመል እረኝነት ያበቃቸውን ህይወት እህ ብየ ሰማኋቸው . . . መርካቶ፤ አብነት ፤ወሎ ሰፈርና ኳስ ሜዳ ተወልዶ አድጎ በዚህ ስራ መሰማራት ምንኛ እንደሚከብድ አሰቡት ! ዛሬ ያ አስገራሚ የወንድም የእህቶቸ ተምር መልቀም ግመል ጠባቂ የመሆን ታሪክም አያስደንቀኝም . . . የባሰ አለ እንዲሉ ከዚህ የባሱ የእህቶቸን የሞት ሽረት የሰቆቃ ኑሮ መስማት ማየት ችያለሁና የካች አምናው አስደንጋጭ ታሪክ ዛሬ ለናንተ እንጂ ለኔ ከባድ አይደለም. . . ሆዳችን ሰፋ አድርገን ማንበብና መስማት ከቻልን ከባዱን ታሪክ ግን በቀጣይነት የምናየው ይሆናል . . .የኔ መነሻ መድረሻ ራሳቸውን ጠቅመው ወገናቸውን ለመደገፍ በኢኮኖሚ ስደተኛ ወገኖቻችን ላይ እየሆነ ካለው እንማር እናውቅበት ዘንድ ፍላጎት አለኝ ! ሰሚም ከተገኘ የመንግስት አካላት፤ የሙብት ጥበቃውና  የሚመለከታቸው ወገኖች መላ ይፈልጉ ዘንድ መረጃ ቅበላየ ከረዳ ደስታየ ወሰን አይኖረውም ! ያ እስኪሆን ግን ወደ በሌላኛዋ የተስፋ ምድር ወደ አረብ ሃገራት የሚሰደዱትን ወገኖቻችን ሰቆቃ ከተጨባጭ መረጃ ጋር ማቅረቡን ግን አሁን አላበቃሁም . . . ይቀጥላል  . . .




ቸር ይግጠመን !

የካቲ 2003 ዓ.ም

**pdfMachine**
**Is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!**
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, if you can print from a windows application you can use pdfMachine.
Get yours now!